# ወይ ንቀት፣ ወይ ጊዜ! (የደብተራው የሳምንቱ ምርጥ ግጥም)

ከመንግስቴ ደፋር

(ፍራንክፈርት - ጃንዋሪ - 2012)

ንገረኝ አልክ አሉ፣ ስረ-መሠረትክን፣
ጥንተ ሥሪትህን፣ አንጋች መሆንህን፣
ሹምባሽ፣ ባንዳነትክን፣ ለጁንታው ማደርክን፣
መንታ ዜግነትክን፣ አረንዛ ሥሪትክን።

ንገረኝ ካልክማ፣ ልንገርህ በወጉ፣
ጥቁር ነው ምላስህ፣ ፈነቢስ ነው ወጉ፣
መሠሪ ነው ልብህ፣ የክህደት መፃጉ፣
አሳሳች ነው መልክህ፣ መንትያ ማረጉ።

አንተው ካመጣኸው፣ ልንገርህ ሥራህን፣
ሾተላይ ነትክን፣ ዘር የማጣፋትክን፣
ሽሽግ  ባንዳነትክን፣ የጎጥ ማቅነትክን፣
በቀትር ነጣቂ፣ ሌት ቀሳፊነትክን።

አንተው ካመጣኸው፣ ንገረኝ ካልክማ፣
በሩቁም በቅርቡም፣ ዝናህ ከናኘማ፣
ክህደትህ ከለማ፣ ሥራህ ከተግማማ፣
ናላህ  ውሉን ስቶ፣ ትንፋሽህ ገለማ!

ወትሮስ መች ፈጥሮብህ፣ ሃቅ ለመናገር፣
ብርዝ ነው መንፈስህ፣ ጅረት የሚሻገር፣
ጥልቅ ነው ተልእኮህ፣ ትውልድ የሚያማትር፣
የወያኔ ሥሪት፣ የደርግ መጢቃ፣ የሻቢያ ደምስር።

ወትሮስ ሀበሻነት፣ ምን ስሜት ሊኖርህ፣
ያደግከው ውረኚ፣ ሥርዓት አልባ ሆነህ፣
የጎጥ ጥንስስ ገፈት፣ የሰው ደም ጨልጠህ፣
ብትገለማ አይደንቅም፣ የደርግ ጡት ጠብተህ።

እንዲህ ነው ልጅ ማለት፣ እንዲህ ነው ማደጎ፣
ሲመሰክር ማየት፣ ባደባባይ ሸንጎ፣
የታሪክ ግማዱን፣ አቻውን ፈልጎ፣
ጥብቅና ይቆማል፣ ላንቃውን ሰንጎ።

በደም የጨቀየ፣ ብእር የተፋውን፣
ወገን የመተረ፣ ህይወት ቀሳፊውን፣
ሀገር ያጠፋውን፣ ትውልድ የፈጀውን፣
ታሪክ ነው ይለናል፣ ናዚ ያቀለመውን።
የቁም ቅዠት ክታብ፣ የጁንታ ኑዛዜ፣
የሌጊዮን ቅጥፈት፣ የክህደት አባዜ፣
የቀሳፊ ምላስ፣ የሀገር ትካዜ፣
ታሪክ ነው ተባልነ! ወይ ንቀት! ወይ ጊዜ!

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ!!!